# በሳውዲ አረቢያ የተደበቁ እውነቶች !
# የቀይ ባህሩዋን ፈርጥ-ጅዳን ያንቀጠቀጠው የዝናብና ጎርፍ !

**ክፍል** 6

ከነቢዩ ሲራክ

ክፍል አምስት መጣጥፌ የት ላይ እንደቆመ አሳምሬ አውቀዋለሁና ግራ አትጋቡ . . . እውነት አላችኋለሁ ቀኑ ሲደርስ እቀጥለዋለሁ . . . የዛሬው ከዚህ በፊት እንደማደርገው የኔው ሰበር ዜና መሆኑን አንድ ካላችሁ ወደ መረጃ ቅበላየ ላቅና . . .

በመካከለኛው ምስራቅ በርሃ ተማክላ በምትገኘው ሳውዲ አረቢያ ጅዳና አካባቢዋ ክረምት የሚሉት ስሙ እንጅ ክረምቱ አይታዎቅም። በጅዳው ክረምት ቅዝቃዜው ከስንት አንድ ማታ ማታ በርታ ቢልም ዝናብ ግን ከአንድ ቀን ባለፈ ሲዘንብ አላስተዋልኩም። ይህ ከ15 አመት ባላነሰው የሳውዲ ቆይታየ የታዘብኩት ነው። በሃገሬ በኢትዮጵያ የሃምሌና ነሓሴ ዶፍ ዝናብ እኝኝ እያለ አላስገባ አላስወጣ ሲል ሲከርም እዚህ ሳውዲ የተገላቢጦች ሃሩሩ እያየለ የሙቀቱ መጠን እስከ 50 ዲግሪ ይደርሳል። ወርሃ ነሓሴ ሃገር ቤት ከርሞ የመጣ አንድ ወንድሜ በጠዋት የአዱ ገነት የሃምሌ ውርጭ አኮማትሮት ከሰአታት በረራ ረፋድ ላይ ጅዳ አውሮፕላን



ማረፊያ ደርሶ እንደወረደ ፊቱን የገረፈው የሙቀት ወላፈን ሲያስደምመው መከረሙ አይረሳኝም። ወንድሜ በሁኔታው ተገርሞና ተደንቆ ከሁለት ሰአት በረራ በኋላ ወላፈኑን ሞቃት የአየር ጸባይ ጅዳ ደረሰ። ሙቀት ሲያላጋው በሰአታት ልዩነት በሁለት ሀገራት መካከል ያየው የተፈጥሮ ጸጋ ልዩነት የገሃነምንና የገነትን ያህል ቢያከብደውም ወደ መጨረሻ በፈጣሪ ድንቅ ስራ ተስማምተን መለየታችን አይዘነጋኝም ። በሃገር ቤት "ብርዱ ምንቴስ ያስተቃቅፋል. . ." በሚባልበት ወቅት በሳውዲ የሙቀቱ ወላፈን ፊትን እየገረፈ አቅልን እንደሚሰውር ማሳየት ከቻልኩ ወደ ሰሞነኛ ወጋወጌ ላቅና . . .

## የታህሳሥ 2003 ዓ.ም የዝናብና ጎርፍ ጥቃት

በሳውዲ የዘንድሮው ክረምት ገብቶ አየሩ ቀዝቀዝ ማለት የጀመረው ገና መስከረም በጠባ ማግስት ቢሆንም ሙቀቱ 30 ዲግሪ ነቅነቅ ያለበትን ጊዜ አልታየም። በህዳር መባቻም ቢሆን የቀኑ ሙቀት እንዳለ ሆኖ ሰማዩ ደንገዝገዝ ብሎ መታየትና አየሩም ወደ ምሽት ቀዝቀዝ ማለት መጀመሩ አስተውለናል። ታህሳስ ሊሸኝ ሲቃረብ ግን አልፎ አልፎም ቢሆን ካፊያ ቢጤ ቦታን እየለየ ፣ማካፋቱ አልቀረም።



ከማለዳ ጀምሮ ተጠናክሮ የሚነፍሰው ነፋስ ነዋሪውን ግራ ያጋባው ያዘ። በአየር ጸባይ መቆጣጠሪያ ሃላፊዎች በኩል 70 ኪሎ ሜትር በሰአት ይወረወር እንደነበር የተነገረው ወበቅና እርጥበት የተቀላቀለበት ነፋስ በሙብረቅና በነጎድጓድ አስፈሪ ድምጽ እየታጀበ የጂዳን የማለዳ ጸሃይ ወደ ደንጋዛ ምሽት ቀየረው ! ታህሳስ መገባደጃ 2003 !

በጂዳ፤ በመካ፤በመዲና፤ በራብቅና በተለያዩ ሰሜናዊ ምእራብ የሳውዲ ክፍሎች የጣለው ከባድ ዝናብ በህይዎትና በንብረት ላይ ጉዳት ማድረሱን የሳውዲ መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት ይፋ አደረጉ. . . ቀጠለና በተጠቀሱት ቦታወች የጣለው ዝናብና ጎርፍ ሀገር ሰላም ብለው ዘመድ ጥየቃ ከቦታ ቦታ በመኪናቸው ውስጥ ሆነው ይንቀሳቀሱ የነበሩ አባትን ከነሁለት ልጆቻቸው የመቅጠፉን ሃዘን መርዶ ሰማን . . . ይህን



መሰሉ አዛዛኝ ዜና የነዋሪውን ልብ ሰበረ ! የዛሬ አመት በተመሳሳይ መንገድ ባንድ ረፋድ በጣለ ዝናብና ጎርፍ አደጋ ከ123 በላይ ህልፈተ ህይዎት ፤ በመቶዎች ለሚቆጠሩት የመቁሰላ አደጋ፤ 11 ሺህ ለሚሆኑ ቤቶች፤ ከ10 ሺህ በላይ ለሚቆጠሩ መኪኖች ከጥቅም ውጭ መሆንና በሚሊዮን የሚቆጠር ንብረት ውድመትን ያስተናገደ ነዋሪና መንግስት ዘንድሮ በሌላ የጎርፍ ጥቃት ማዕበል መናጥ በጀመረ ቅጽበት ለህልፈተ ህይወት የተዳረጉት አባትና ልጆች ታሪክ ከታች አምናው ጎርፉ አደጋ ጋር ሲመዛዘን ጉዳቱ የሚማረር አልሆነም.

**pdfMachine - is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
**Get yours now!**
"Thank you very much! I can use Acrobat Distiller or the Acrobat PDFWriter but I consider your product a lot easier to use and much preferable to Adobe's" A.Sarras - USA

. . ይህ ሆነና ልጆቹን ከውሃ ጥፋት ሊያድን አንዱን ይዞ አንዱን መጨበጥ አቅቶት ከነራሱ መውጫ አጥቶ ደፋ ብሎ የቀረውን አባትና የልጆች ቅስፈት መሪር ሃዘን በጸጋ መቀበል የግድ ሆነ ! ተመስገን ተብሎ ቀን ተገፋ . . . በጎርፍ ጥቃቱ የወደመውና በሃብትና ንብረት ላይ ያደረሰውን ኪሳራ ግን ቤት ይቁጠረው ከማለት ውጭ ምንም ማለት አይቻልም ! የጎርፍ አደጋ ለመከላከል በተንሳፋፊ ፕላስቲክ ጀልባወችና በሂሊኮፕተር በመታገዝ በተደረገው የነብስ ማዳን ጥረት 219 ነዋሪዎችን ከተለያዩ ቦታዎች ከአደጋ ለመታደግ መቻሉን የሳውዲ ልኡላን ሲያስታውቁ መንግስት አደጋውን ለመከላከል አስፈላጊውን ዝግጅት እንዳደረገና ሁኔታዎች በቁጥጥር ስር ማዋላቸውን አስታዎቁ ::

[

## ማየት ማመን . . .



ይህ ሁሉ ሲሆን የአየሩ ሁኔታ አስተማማኝ አለመሆኑን የሳውዲ መንግስት የአየር ትንበያ ሃላፊዎች ማስጠንቀቂያ በተንቀሳቃሽ ስልክ (በሞባይል) መልዕክት አሰራጭተው ነበር፡፡ የአየር ጸባይ ትንበያውን መሰረት በማድረግ የሳውዲ አየር መንገድ አለም አቀፍና የሃገር ውስጥ በረራ መቋረጡ ተነገረ፡፡ በአደጋው ችግር የሚደርስባቸው ለመርዳት የመንግስትና የግል ሆስፒታሎች አስፈላጊውን ዝግጂት ማድረጋቸውን የጤና ጥበቃ ሚኒስትር በበኩሉ ባወጣው መግለጫ አስታውቀዋል፡፡ በመልዕክቱ ቀይ ባህር የሚያዋስናቸው ከተሞችን ጨምሮ በሰሜናዊ ምእራብ የሃገሪቱ ክፍሎች መጠኑ ከፍ ያለ ዝናብ እንደሚጥል ሲያስታውቁ ነዋሪዎች ከቀይ ባህር ዳርቻ ብዙም እንዳይቀርቡና አደገኛ ተብለው ከሚመከሩ ቦታችው መጠንቀቅ እንደሚገባ መከሩ. . . ዘከሩ . . . የሰሙ ተጠቀሙ ፤ ያልሰሙ በወጡበት መንገድ ተዘግቶባቸው የሚይዙት የሚጨብጡት ሲያጡ ተስተዋለ፡፡. . . በከተማዋ በጅዳ በተለያዩ ቦታወች ከባድ የሚባል ዝናብ ሲጥል በአንዳንድ ቦታወች ደግሞ ጸሃይ ተስተዋለ . . . እንደ ትንብያው ዝናብ አለመስተዋሉ ያዘናጋቸው ወገኖች ትንበያው አጣጣሉት . . . አጣጥለውም ከአካባቢያቸው ያልራቁት ተጠቀሙ . . . ከአካባቢያቸው የራቁት መንገድ ተዘግትባቸውና የሚላወሱበት አጥተው በራሳቸው ሰአት ያመጡትን ችግር መቋቋም ነበረባቸውና ማየት ማመን መሆኑን ሳይወዱ በግድ ተረዱ !

## ኢትዮጵያውያንና ጎርፉ . . .

የጠቆረው ሰማይ ውስጥ የሚስገመገም ድምጽ ይሰማል . . . አስፈሪው ነጎድጓድ ጥቁር ደመናውን እየሰነጠቀ ግርማ ባለው ድምጹን ከአንጸባራቂ ብልጭታው ጋር እየቀላቀለ ዶፍ ዝናቡን ያወረደው ጀምሯል . . . ከፍተኛ ዝናብ ካጠቃቸው አካባቢዎች መካከል በጂዳ ደቡባዊ ክፍል የሚዋሰነው የኢትዮጵያ አለም አቀፍ ትምህርት ቤት አንዱ ነበር፡፡ ምንም እንኳን ለመላ ነዋሪው የተሰራጨውን መልዕክት ለትምህርት ቤቱ ባለቤት ለኮሚኒቲውና ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር ደርሶ ቅድሚያ ጥንቃቄ ለማድረግ ትምህርት ቤቱን መዘጋት የነበረበት ቢሆንም በዚህ ረገድ መዘናጋት እንደከሰተ መናገር ይቻላል፡፡ ያም ሆኖ ዝናብ የመጣል አዝማሚያ ሲታይና ሰማዩ በመብረቅ ሲናጥ የተመለከቱ የትምህርት ቤቱ አስተዳደርና ሰራተኞች የወሰዱት አፋጣኝ እርምጃ የሚበረታታ ነበር፡፡ ስራ ላይ እንዳለሁ ከትምህርት ቤት ተደወለልኝና እኔም የቻልኩትንም ያህል መልዕክት ለወላጆች አሰራጭቸ ብላቴና ልጆቸን ከት/ቤት ላመጣ ወደ ዚያው አቀናሁ . . . ዝናቡ መዝነብ ጀምሯል . . . ዝናብ አይተው የማያውቁት የተለያዩ አረብ ሃገራት ተወላጆችና ሳውዲ ወጣቶች ደስታቸው ወሰን አጥቷል . . . አብዛኛው 4x4 (ላንድ ክሩዘር የምንለው አይነት አውቶሞቢል መሆኑ ነው) በዘመናዊ አውቶሞቢሎቻቸው በየአውራ መንገዱ በታቆረው ውሃ እየገቡ በደስታ ይንፏለሉ ይዘዋል . . . ቁመቷ ከፍ ያለችው አሮጌ ቶዮታ የኔዋ 4x4 ናፍጣ አውቶሞቢልም ለዚህ መሰሉ ቀን እንደማትጥለኝ ካንድም ሁለቴ አሳይታኛለችና ልቤን ደልደል አድርጌ መንገዱን አቆራርጬ ት/ቤት ደረስኩ፡፡ ሳውዲ ተወልደው ያደጉት ኢትዮጵያውያን ህጻናትም ዝናብ እንደማያውቁት አረቦች ዝናቡ ብርቅ ሆኖባቸው እየቦረቁ በውሃ ሲንቦጫረቁና ሲጫዎቱ አጋጠመኝ. . . እንዴት እንደምመለስ ሳውጠነጥን ናላየ የዞረ ጎልማሳ አባት የልጆቸንና የጓደኞቻቸውን ደስታ ስመለከት "አይ ልጅነት . . . !" ብየ ብቻ አልተከዝኩም . . .በሌላ ሃሳብ ተወሰድኩ . . . የትምህርት ቤቱን መራቅና በደህናው ጊዜ እንኳ ሰባራ አውቶሞቢልን እያንተፋተፍን ሩቁን መንገድ ባሳር የምንደርስ ወላጆችንና በልጆችን ዙሪያ ማሰብ ያዝኩ . . . እኔ አላዋቂው ቀርቶ ያወቁ የነቁት አለ በሚሉት የትምህርት ቤቱ ችግር ከፊቴ ክችም አለብኝ . . . ብዙ ሄድኩ . . . መቀጠል ግን አልቻልኩም. . . መልዕክት ደርሷቸው በጊዜ ወደ ትምህርት ቤቱ እንደኔው የመጡ ወላጆች እስከነ ጫማቸው በሚወርደው ዶፍ ዝናብና በታቆረው ውሃ እየተራጩ ከወዲያ ወዲህ የሚዘሉ የሚቦረቁ ልጆቻቸውን እየታገሉ በመያዝ መንገድ ሁሉ ሳይዘጋጋ በቻሉት ፍጥነት አፈተለኩ . . . የትምህርት ቤቱ አስተዳደርና ሰራተኞች ሙሉ ቀን በትምህርት ቤቱ ሆነው ተማሪዎችን ወደየቤታቸው ሲያሰማሩ በመዋላቸው ተጠቃሽ ችግር ሳይከሰት ያ ቀን ተሰናበተ . . . በአካባቢው በምንኖር ኢትዮጵያውያን መካከል ሆነ አንድ ቀለም አንድ የዘር ግንድ ያለን ግን በተለያየን በኤርትራዉያኑ ወገኖቻችን ዙሪያም ቢሆን የከፋ አደጋ ስለመድረሱ መረጃ የለም ! ሁሉም ሰላም ነው አሉ !

**pdfMachine - is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
**Get yours now!**
"Thank you very much! I can use Acrobat Distiller or the Acrobat PDFWriter but I consider your product a lot easier to use and much preferable to Adobe's" A.Sarras - USA

## የጥር 18 ቀን 2003 ዓ.ም ሌላ የዝናብና ጎርፍ ጥቃት



በጎርፍ የሞቱት የአባትና ልጆች አርባ ሳይወጣ ባሳለፍነው ጥር 18 ቀን 2003 ዓ.ም ረቡዕ ረፋዱ ላይ ከአምስትና ስድስት ሰአታት በላይ የቆየው የዝናብ ውርጅብኝና የጎርፍ አደጋ የጅዳን ከተማ አማክሎ ያጠቃት ገብቷል . . . ዝናቡና ያስከተለው ጎርፍ ለአራት ሰዎች መሞት ምክንያት ሲሆን በሚሊዮን በሚቆጠር ንብረት ላይ ጉዳት ማድረሱን የሳውዲ መንግስት ባለስልጣናትና በተለይም የጂዳ መካና ሙከረማ አገረ ገዥ ልኡል ካልድ አል ፋይሰል በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ይፋ አድረገዋል፡፡ አደጋውን ተከትሎ ለነዋሪው አስፈላጊው ሁሉ እርዳታና የድጋፍ እርዳታ ይደረግላቸው ዘንድ የሳውዲ መራሄ አሚሮችን ጨምሮ ከቀዶ ህክምናቸው በኋላ በእረፍት ሞሮኮ የሚገኙት ንጉስ አብደላ ቢን አብድላዚዝ ጥብቅ ትዕዛዝ ማስተላላፋቸውን ልኡል ካልድ ጠቁመዋል፡፡ በጎርፍ የተጎዱ ቦታዎችን በሂሊኮፍተር ተዘዋውረው የጎበኙት ልኡል ካልድ መንግስት ሁኔታውን ለመቆጣጠር አስፈላጊውን ሁሉ እርምጃ በመውሰድ ላይ መሆኑን ሲያስታውቁ የጣለው ዝናብ መጠን 113 እስከ 120 ሚሊ ሜትር እንደሚደርስና በየትኛው ቦታ ቢሆን መጠኑ ከሚጠበቀው በላይ መሆኑን በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫቸው አስታውቀዋል፡፡ ልኡል ካልድ በዚሁ መግለጫቸው አደጋው በሰው ህይወትና በንብረት ላይ ስላደረሰው አደጋና መንግስት በማድረግ ላይ ስላለው የአደጋ መከላከል ጥረት ዝርዝር መረጃ ሰጥተዋል፡፡



በጎርፉ አደጋ በከፍተኛ የተጎዱት አከባቢዎች ሃይል ተውፊቅ ፤ ሳምር ፤ ነኽሂል ፤ አመል ከይር፤ ሸረፍያ፤ከንደራ፤ጉዌዝ፤ ባግዳድያና ሃምራ የተባሉ ቦታዎች መሆናቸው ተጠቁሟል፡፡ እስካሁን ባለው መረጃ መሰረት በአደጋው የሞቱት ሰዎች ቁጥር አራት መሆኑና ከሞቱት መካከልም የሳውዲ የየመን የግብጽና የቱርክ ዜጎች እንደሚገኙበት በሃላፊዎች ቢገለጽም አምስተኛ ሰው መሞቱን መገናኛ ብዙሃን ዛሬ በዘገባቸው አስታውቀዋል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን እስከ ትናንት ሃሙስ ምሺት ድረስ በአደጋ መከላከያ ቡድን 466 ነዋሪዎችን በሂሊኮፕተርና መኪና በሚገባባችው ቦታወች የነበሩ 951 ያህል ነዋሪዎች እርዳታ በማድረግ ወደ አስተማማኝ ቦታወች መወሰዳቸውን ታውቆዋል፡፡ በአደጋው በርካታ ማህበራዊ ግልጋሎት ስራ መሰናከላቸውን የገለጹት ልኡል ካልድ ከጣለው ዝናብ አንጻር የአሁኑን የጎርፍ አደጋ ለመከላከል ከባድ ቢሆንም በከተማዋ በመሰራት ላይ ያሉት የውሃ ማስተላለፊያ ቧንቧዎች አለመጠናቀቅ ችግሩን እንዳባባሰው አልደበቁም፡፡ በዚህ ረገድ የውሃ ማስተላለፊያ ስራው 10 እጁ ብቻ መጠናቀቁንና ለታየው የስራ መጓተት ልኡሉ ነዋሪውን ይቅርታ ጠይቀዋል፡፡ ልኡል ካልድ በማከልም ችግሩን ለመቅረፍ በመንግስት በኩል ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው በመሆኑ አስፈላጊ ስራዎች በመቀላጠፍ ላይ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡



ላለፉት 17 አመታት ታይቶ የማይታወቅ እንደሆነ በተነገረው ዝናብ የከተማዋን ዋና ዋና መንገዶች በውሃ ተሞልተውና ተዘግተው የታዩ ሲሆን በርካታ አውቶሞቢል ተበላሽተው እንዲቆሙና በአንዳንድ ቦታወችም በጎርፍ ሲዎሰዱም ተስተውሏል፡፡ በስራ በትምህርትና በተለያዩ ምክንያት በማለዳው ከቤታቸው የወጡ ነዋሪዎች መመለሻ አጥተው ሲንከራተቱ የተስተዋለ ሲሆን አንዳንዶች ለሰአታት ተጉዘው ቤተሰቦቻቸውን ተቀላቅለዋል፡፡ በተለይም ሁኔታው አላላውስ ብሎዋቸው የዋሉት ትምህርት ቤቶች በተቻለ መጠን ተማሪዎችን ወደየቤታቸው ለማሰማራት ሲሞክሩ



መንገድ የተዘጋባቸው በየሰው ቤት ተጠልለው ማሳለፋቸውን የአይን ምስክር እሆን ዘንድ ከመስማትም ለመመልከት ችያለሁ፡፡ የዚህ መሰል ችግር ዳፋ ቀማሽ የሆኑት በጅዳ ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ነዋሪዎችና የኢትዮጵያ አለም አቀፍ ትህርት ቤት ተማሪዎች ለሰአታት እንቅስቃሴያቸው ተገትቶ እንደነበር ለመረዳት ተችሎዋል፡፡ ከሰአታት በኋላ ትምህርት ቤቱና ወላጆች ባደረጉት ቅንጂት አብዛኛው ተማሪዎች ወደየቤታቸው ለማሰማራት የተቻለ መሆኑ ሲታወቅ መንገድ በመዘጋቱ በተፈጠረው መጨናነቅ ህጻናትን ይጓዙባቸው የነበሩ

**pdfMachine - is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
**Get yours now!**
"Thank you very much! I can use Acrobat Distiller or the Acrobat PDFWriter but I consider your product a lot easier to use and much preferable to Adobe's" A.Sarras - USA

አውቶሚቢሎችም እንቅስቃሴ በጎርፍ በመገታቱ እንግልት እንደደረሰባቸው ነዋሪዎችና የትምህርት ቤቱ ሹፌሮች አጫውተውኛል፡፡ ታዳጊና ህጻናት ተማሪዎችን ይዘው መንገድ የተዘጋባቸው አውቶሞቢሎች ሲሰናከሉ በድልድይ ስር ለማደር የተገደዱም ነበሩ፡፡ እድሉ የቀናቸው ግን የሳውዲ አደጋ መከላከያ ሂሊኮፕተር እርዳታን አግኝተው ከአደጋ የተረፉ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች እንደሚገኙበት አንዳንድ ከአደጋ የተረፉ ወላጆች በስልክ ገልጸውልኛል፡፡ በአደጋው ከተጎዱ አካባቢዎች የመጡ ወደ ሰላሳ የሚጠጉት ተማሪዎች ወደ ቤታቸው መሄጃ መንገድ በመዘጋጋቱ መጠለያ ፍለጋ ወደ ኢትዮጵያ ቆንስል መስሪያ ቤት በመሄድ በኮሚኒቲው ካፊቴሪያ መጠለላቸውን ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ረቡዕ እኩለ ሌሊት ወደ ኮሚኒቲው ካፍቴሪያ በመሄድ ተማሪዎችን ያነጋረርኩ ሲሆን በዚህ አጋጣሚ ጉዳያቸውን ለማስፈጸም ወደ ቆንስል መጥተው መንገድ በመዘጋቱ እዚያው አዳራሽ ለማደር የተገደዱ ነዋሪዎችን ጭምር አግኝቸ ስለሁኔታው አስረድተውኛል፡፡



መጠለያ ፈልገው ወደ ኢትዮጵያ ቆንስል የኮሚኒቲ ካፍቴሪያ የመጠለላቸው ወሬ እንደተሰማ አንዳንድ ነዋሪዎች የተቸገሩትን ተማሪዎች ወደ የቤታቸው በመውሰድና ከቤተሰባቸው ለማገናኘትና ያደረጉት መልካም ሰብአዊ ትብብር በዚህ መሰሉ ጭንቅ ሰአት የታየ ወገናዊ አኩሪ ተግባር ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ተማሪዎችን ለመውሰድና ለቀሩት ራት የሚሆን ምግብ ወተትና ጭማቂ ሲያቀርቡ ያገኘኋቸው ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የወላጅ ኮሚቴ አባልና ባለቤታቸው ተማሪዎችንና ወላጆችን ስልክ በመደወል ሲያገናኙም ተመልክቻለሁ፡፡ ተማሪዎችንና ነዋሪዎች ሲደግፉ ከዋሉት የካፍቴሪያው ሰራተኞችና መካከል ያነጋገርኳቸው የኮሚኒቲ ሰራተኞች ለተማሪዎች ለወላጆችና ለባለጉዳዮች ራትን ጨምሮ የሚጠጣ በማቅረብ የተቻላቸውን ትብብር ሲያደርጉ መዋላቸው ከአንድ ዜጋ የሚጠበቅ እንጂ የሚጋነን እንዳልሆነ ትህትና በተሞላበት ስነ ምግባር የገለጹልኝ ሲሆን አንዳንድ ወላጆች ተማሪዎችን ከወላጆቻቸው ለማገናኘት ባደረጉት ሙከራ መደሰታቸውን አጫውተውኛል፡፡

ዛሬ ሁኔታዎች ተረጋግቷል. . . ተማሪዎች ወደ የቤታቸው በመሄድ ከቤተሰባቸው ጋር መቀላቀላቸው ለመረዳት ችያለሁ . . . ዋና ዋና መንገዶች ግን አሁንም እንደተዘጉ ነው፡፡ ሁኔታው እስኪረጋጋ በሚል የሳውዲ መንግስት ትምህርት ቤቶች የአንደኛ ክፍል ተማሪዎቻቸው ትምህርት ለሳምንት መዘጋቱን የትምህርት ሚኒስቴር ሲያስታውቅ የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች ግን ከነገ በስቲያ እሁድ ትምህርታቸውን እንደሚጀምሩ አስታውቀዋል፡፡ የኢትዮጵያ አለም አቀፍ ትምህርት ቤት በአንጻሩ ቅዳሜ ጥር 21 ቀን 2003 ዓ.ም ለአንድ ቀን ብቻ ትምህርት ቤቱን እንደተዘጋ ሃላፊዎቹ ገልጸውልኛል፡፡ ይህ ሲሆን የመንግስት ተወካዮቻችን በቦታው አልተገኙም. . .የተቸገሩ ተማሪዎችና ባለጉዳዮች በኮሚኒቲው አዳራሽ ውለው ሲያድሩ አያውቁም አይባልም ! መረጃ መስጠቱም ሆነ የአይዟችሁ የወገናዊነት ድምጻቸው አለመሰማቱ ግራ ያጋባው ግን እኔን ብቻ አልነበረም ! ምክንያት ከተገኘ ጥሩ ! ብቻ. . . እንደተለመደው ወገን ለወገን በዚህ ክፉ ቀን ያሳየውን ድጋፍ ግን ዛሬም ሆነ ነገ ሊቀጥልበት ይገባል እላለሁ !
የነገውን ነገ እንሰማለን . . . ለዛሬው የሰማነውን በልቦናችን ያሳድርልን !

ቸር ይግጠመን

**pdfMachine - is a pdf writer that produces quality PDF files with ease!**
**Get yours now!**
"Thank you very much! I can use Acrobat Distiller or the Acrobat PDFWriter but I consider your product a lot easier to use and much preferable to Adobe's" A.Sarras - USA